*ቀን 12/03/2005 ዓ.ም*

*ለሚሺሪያ መጽሔት ዋና አረጋጅ!*

*<u>አዲስ አበባ</u>*

*ጉዳዩ <u>የኅዳር 2005 ዓ.ም «ኦርቶዶክስና እና ተዋሕዶ» በሚል ርእስ ስለወጣዉ ጽሑፍ ይመለከታል፡</u>*

*ሰላሙንና ጤናዉን፣ ትጋቱንና ቅድስናዉን፣ ጽድቁንና መንግሥቱን፣ ባጠቃላይ መልካሙንና የእግዚአብሔርን መንግሥት የምመኝልዎ የዚህ መጽሔት ዋና አዘጋጅ ኤደን ሸዋ፤ ይህን ደብዳቤ እንድጽፍሎዎ ያስገደደኝ በኅዳር 2005 ዓ.ም ላይ ሚሺሪያ በሚል መጽሔት ላይ ከላይ በተገለጸዉ ርእስ ስር ስለ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶና ስለ ቅዱስ ነቢዩ ኤልያስ ከሰማይ መዉረድ በተመለከተ አባ ዮሴፍ ከተባሉ ወንድም ጋር ያደረጋችሁትን ቃለ መጠየቅና መልስ፤ የኢትዮጵያ ትንሣኤ የሚጠባበቁትን ለመከፋፈል ዋና ጠላታችን ዲያብሎስ በረቂቅ መንገድ እንዳመጣዉ ተስምቶኝ ነዉ፡፡ ይኸዉም «ሣልሣዊ ቴዎድሮስ» በመባል የሚጠበቁ በኢትዮጵያ ትንሣኤ ዘመን ርእሰ ነገሥት(ንጉሠ ነገሥት) የሚሆኑ እንዳሉ ሁሉ፤ አሁን ደግሞ በመጽሔቱ ላይ አባ ዮሴፍ የተባሉት «ርእስ ነቢያት ወ ነገሥት ቅዱስ ኤልያስ ከሰማይ ወርዷል እና እርሱን ተቀበሉ፤ የሚላችሁን አድርጉ» እያሉ ነዉ፡፡ እግዚአብሔር ደግሞ ሁለት እንደራሴዎችን በአንድ ጊዜ ሊያስነሳ አይችልም፡፡ አንደኛዉ እዉነትኛ አንደኛዉ ሐሰተኛ ነዉ፡፡ ዲያብሎስም በሐሰተኛዉ እንደራሴ በመጠቀም አማኙን ለሁለት ለመክፈል ቆርጦ እንደተነሳ ነዉ የሚያሳየን፡፡ እንደ መሳሪያም የሚጠቀምባቸዉ ደግሞ የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮችንና አማኞችን ነዉ፡፡ ስለዚህ እዉነተኛዉን እንደራሴ እናንተም ሆናችሁ ሌላዉ ሕዝብ እንዲለይ ለማስቻል ነዉ የእዉነተኛ እንደራሴዎች መለያ ጠባያቸዉና ሕይወታቸዉን በአጭሩ የምገልጸዉ፡፡ ምክንያቱም የእያንዳንዱ ተግባርና ፍሬ እንዲሁም ሕይወት ነዉ ማንነቱንና ምንነቱን የሚገልጽልን፡፡ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስም በመዋዕለ ሥጋዌዉ ሐሰተኞቹን ከእዉነተኞቹ የሚለዩበት ከፍሬያቸዉ መሆኑን በሚገባ አሳዉቆናል፡፡*

*ለእናንተ ብቻ አይደለም ሌሎችም ይህን ጉዳይ እንዲያዉቁት በተለያየ አድራሻቸዉ (በኢሜላቸዉ) በይፋ ግልጽ ያደረኩላቸዉ፤ እናንተም በመጽሔታችሁ ጉዳዩን በይፋ ለሁሉም ግልጽ ስላደረጋችሁት ነዉ፡፡ ሌላዉ እንድጽፍላችሁ ያስገደደኝ፤ ይህን መጽሔት ባነበብኩ ማግስት ደግሞ በኅዳር ሰባት 2005 ዓ.ም በቅድስት ሥላሴ የማታ መርሐ ግብር ላይ ስብከት*

ስከታተል፤ በዕለቱ ረፋዱ ላይ ሰዎችን አስከትሎ «ነቢዩ ኤልያስ ነኝ» ብሎ በቤተክርስቲያን ዙሪያ ሲሰብክ የነበረ ሰዉ እንዳጋጠማቸዉና ምእመኑ እንዳይሰናከል ማሳሰቢያ ሲሰጡ በመስማቴ ነዉ:: እኔም ሳይገባኝ የእዉነት ምስክር እንድሰጥ እግዚአብሔር ከመስከረም 2003 ዓ.ም ጀምሮ ያስነሳኝ ኢትዮጵያዊ የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት ቤተሰብ ስለሆንኩ፤ ወገኖቼ ኢትዮጵያዉያን ሆኑ የአዳምና ሔዋን ዘሮች በተኩላ እንዳይበሉ እግዚአብሔር የሚያናግረኝን እናገራለሁ፣ የሚያሰራኝን እሰራለሁ:: በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ያሳሰበኝን ለዓለም እገልጻለሁ::

በቃለ መጠይቃችሁ ላይ ከበቁ አባቶች በደረሳቸዉና መንፈስ ቅዱስ በገለጠላቸዉ መሰረት ጳጉሜ፩÷፳፻፫ (1/13/2003) ዓ.ም ርእሰ ነብያት ወነገሥት ቅዱስ ኤልያስ ወደ ምድር መዉረዱን አስነብባችኋል:: እንዲሁም እሁድ ሰንበተ ክርስቲያን በአይሁድ ሰንበት ቅዳሜ መተካታ እንዳለበትና ሰንበት ቅዳሜ ብቻ እንድትሆን ትልቁ የቅዱስ ነቢዩ ኤልያስ መልእክት እንደሆነ ተገልጿል:: ቅዳሜን ለማስቀረት የሚፈልግ ሰዉ በእግዚአብሔር ላይ ዓመፅ የሚያነሳ ነዉ ተብሎ ተገልጿል:: እሁድ ሰንበት የተባለችሁ ጣዖት አምላኪዎች ሆን ብለዉ ዕለቱ እንዲከበርላቸዉ ፈልገዉ እንደሆነ ተገልጿል:: ሌሎቹ ፍሬ ሐሳቦች አብዛኛዉን የምቀበላቸዉ ስለሆነ ስለ እነሱ አስተያየት የምሰጠዉ የለም::

ለመሆኑ ስንት አምላክ አለ? ስንት መንፈስ ቅዱስ አለ? አንድ አምላክ አንድ መንፈስ ቅዱስ ብቻ አይደለም ወይ ያለዉ? ለምን የሥጋና ደም ስሜታችንን በእግዚአብሔር እዉነት ዉስጥ እንደባልቃለን? ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ የሚፈትነን እንደ እምነታችን ደረጃ ነዉ እንጂ፤ እኔን መሰሉን ተራዉን ምእመን የሚፈትነዉና ዋሻ የዘጋዉን እንዲሁም ራሱን ፍጹም አድርጎ ብቃት ደረጃ ላይ ያደረሰዉን እኩል አይፈትንም:: በተለይ ራሱን ፍጹምነትና ብቃት ደረጃ ላይ እንደደረሰ አድርጎ የሚቆጥረዉን በትዕቢቱና በአንድ ክፍተት በመግባት ከሕይወት መንገድ ያወጡታል:: እሱም ተሰናክሎ ሌላዉንም ያሰናክላል:: ለመሆኑ ነቢዩ ኤልያስ ሥጋ ለብሶ ነዉ ከላይ በተጠቀሰዉ ቀን ከሰማይ ወርዶ በዚህ ምድር የተገለጸዉ? ወይስ የመላእክትን አካል ለብሶ ነዉ የተገለጸዉ? ከተገለጸስ እስከ አሁን ድረስ ምን እየሰራ ነበር? አሁንስ ምን እየሰራ ነዉ? እግዚአብሔር በአሁን ዘመን በምድር ካሉት ሰዎች እንደ ነቢዩ ኤልያስና ከዛም በላይ እንደ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ዓይነት ማስነሣት ያቅተዋልን? ድርሻዉን በሚገባ ተወቶ ወደ አምላኩ እቅፍ የሄደዉ ቅዱስ ኤልያስ ዳግም ወደዚህች የከረፋች ዓለም ዉስጥ እንዲኖርና እንዲያገለግል እግዚአብሔር ይልከዋልን?

*ያለዉ እዉነት ከነሐሴ 18/2004 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ኅዳር12/2005 ዓ.ም ድረስ «ታላቅ የብርሃን ተስፋ ለኢትዮጵያዉያንና ለዓለም ሕዝብ» በሚል ርእስ በተጻፈዉ ሦስተኛዉ የእግዚአብሔር መልእክት ላይ ስለ ነቢዩ ኤልያስ ሆነ ስለ ጻድቁ ሄኖክ ወደ ምድር ይመጣሉ ስለሚባለዉ እዉቀት እግዚአብሔር በግልጽ ምላሽ ሰቶበታል። እሱን ብቻ አይደለም ስለ ሰንበት በደንብ ተገልጿል። አባ ዮሴፍ ሆኑ ሌሎች የበቁ አባት የሚሏቸዉ ሊቆሙና ሊመሰክሩለት የሚገባዉ ስለ ሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት ነዉ እንጂ ዳግም የጻሕፍት ፈሪሳዉያን፣ የአይሁድ ካህናት የዓመፃ ሕይወት አይደለም። እግዚአብሔር በአሁን ሰዓት ልዩ አገልጋይና መልእክተኛ አድርጎ ያስነሣቸዉ ሰዎች ደግሞ፤ በዓለም ዉስጥ ሆነዉ ራሳቸዉን ሳይገልጡ ሰዉረዉ ያሉ እንደማንኛዉም ሰዉ ከወላጆቻቸዉ ተወልደዉ አገራቸዉንና ቤተክርስቲያናቸዉን በተለያየ መንገድ እያገለገሉ ያሉ እንደ እኛዉ ምድራዊ ሰዉ የሆኑ ከሰማይ ያልመጡ፤ ነቢያትን፣ ሐዋርያት፣ ሰማዕታት፣ ጻድቃንን ይመራ የነበረዉ አንዱ መንፈስ ቅዱስ የሚመራቸዉ፤ «ሣልሳዊ ቴዎድሮስ» በመባል የሚጠበቁ እጅግ በቅርቡ በሚመጣዉ በኢትዮጵያ ትንሣኤ ለእግዚአብሔር ሕዝቦች ጠባቂነትና አገልጋይነት በሥጋዊ ወንበር ላይ ተቀብተዉ የሚቀመጡ የእግዚአብሔርና የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ባላሚልና እንደራሴ የሆኑት ርእሰ ነገሥት (ንጉሠ ነገሥት)፤ እንዲሁም በኢትዮጵያ ትንሣኤ ለእግዚአብሔር ሕዝቦች ጠባቂነትና አገልጋይነት የእግዚአብሔርና የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ባላሚልና እንደራሴ ሆነዉ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ የሚቀመጡት ርእሰ ሊቃነ ካህናት እጨጌ(ፓትርያርክ) ናቸዉ።*

*እረኛዉ አንድ መንጋዉ አንድ በመሆንበት ሰዓት በመንፈስ ቅዱስ ብቻ ተመርተዉ የሚወስኑትን ሆነ ለዓለም ግልጽ የሚያደርጉትን የእግዚአብሔር ሙሉ እዉነት፤ የትኛዉ ቅዱስ ወይንም የበቃ ሰዉ ነዉ «የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት በስህተት ነዉ እሁድን እንደ ሰንበት የምታከብዉ፤ ትክክለኛዉ ሰንበት ቅዳሜ ብቻ ነዉ» የሚለዉ? መሪያቸዉ አንድ መንፈስ ቅዱስ የሆነ ሁሉ አቀራረባቸዉ፣ እዉቀታቸዉ፣ ጥሪያቸዉ፣ ብቃታቸዉ ይለያያል እንጂ ዓለማቸዉና ግባቸዉ እንደ ነቢያት፣ ሐዋርያት፣ ሰማዕታት፣ ጻድቃን አንድ የሆነ ብቻ ነዉ። በመሆኑም ከላይ የተገለጹት የእግዚአብሔር ባለሚሎችና እንደራሴዎች በሥጋዊና በመንፈሳዊ ወንበር ላይ ቢቀመጡም ዓላማቸዉና ግባቸዉ አንድ የሆነ፤ ይኸዉም ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ እግዚአብሔር ለሰዉ ዘሮች የሰጠዉን ሰባቱን ቅድሳት ኪዳናትን መጠበቅና ማስጠበቅ ነዉ። «የእግዚአብሔር ሰዉ ነኝ፣ መልእክተኛ ነኝ፣ እዉነተኛ አገልጋይ ነኝ» የሚል ሁሉ መሪዉ አንዱ መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ ስለ ቅዱሱ ኪዳን ነዉ ምስክርነት*

የሚሰጠዉና ተጋድሎ የሚያደርግለት እንጂ «የብሉይ ኪዳን ቅዳሜ ሰንበት ትከበር የሐዲስ ዘመን ሰንበት እሁድ ትሻር» አይልም።

በመሆኑም አታላዩ(ሸዋጁ) መንፈስ የብርሃን መልአክ መስሎ እንደሚያሰናክልና እንደሚያሳስት አባ ዮሴፍ ሆኑ ሌሎች አባቶች በሚገባ አስተዉለዉ ለእግዚአብሔር ሙሉ እዉነት እንዲሰለፉ የቀደሙትን የእግዚአብሔር መልእክቶች በእኔ በኩል ለኢትዮጵያዉያንና ለዓለም ሕዝብ የተላለፉትን «የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ» በሚል ርእስ መስከረም 2003 ዓ.ም የተጻፈዉን የመጀመሪያን መልእክት፣ «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ ከመስከረም እስከ ታሕሳስ 2004 ዓ.ም የተጻፈዉን ሁለተኛ መልእክት፣ እንዲሁም አሁን ከነሐሴ 18/2004 እስከ ኅዳር 12/2005ዓ.ም የተጻፈዉን ሦስተኛ የእግዚአብሔር መልእክት፣ ከዚህ በተጨማሪ በሣልሳዊ ቴዎድሮስ በኩል «ኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን» በሚል ርእስ ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ እስከ መስከረም 21/2004 ዓ.ም ድረስ የተጻፈዉን አራት የእግዚአብሔር መልእክታትን የያዘ፣ እንዲሁም በተለያየ ጊዜ በእኔ በኩል የተላለፉ መልእክቶችን ለእናንተም ሆነ ለአባ ዮሴፍ በሲዲ አድርጌ ከዚህ ደብዳቤ ጋር በአድራሻችሁ ልኬላችኋለዉና ሁሉንም ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻዉ ድረስ በትዕግስት አንብቡት። ያኔ ወደ እግዚአብሔር ሙሉ እዉነት ትደርሳላችሁ። እናንተም አትሰናከሉም፤ ሌላዉንም አታሰናክሉም።

ሌላዉ ለመግለጽ የምፈልገዉ ቀደም ሲል እንዳሳወኩት፤ የእግዚአብሔርና የእመቤታችን ባለሟሎችና እንደራሴዎች ራሳቸዉን «ነቢዩ ኤልያስ ነኝ፣ ቅዱስ ነኝ፣... ወዘተ» የሚል ስያሜ ለራሳቸዉ ሊሰጡ ይቅርና ራሳቸዉን እንደ አገልጋይ እንኳ የማይቆጥሩ፣ የበዛላቸዉን ጸጋና ሥልጣን ከቁም ነገር ሳይቆጥሩ «ተራ፣ ወራዳ፣ ኃጢአተኛ፣ አቧራ፣ ለምንም የማልጠቅም፣... ወዘተ» እያሉ ነዉ በእግዚአብሔር መልእክት ላይ ማንነታቸዉን ያስተዋወቁት እንጂ፤ አንድም ቀን ራሳቸዉን ክበዉና ተከታይ ለማፍራት «እንዲህ ነኝ» ብለዉ ራሳቸዉን አልገለጹም። እግዚአብሔር ከገለጸለት ሰዉ ዉጭ ማንም የማያዉቃቸዉ፣ «እንዲህ ናቸዉ» ተብሎ እንዲነገርላቸዉ የማይፈልጉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ የሚፈጽሙና የሚያስፈጽሙ ናቸዉ።

ሌላዉ እንዲታወቅ የምፈልገዉ እነዚህ እንደራሴዎች፤ ወደ ወንበር የሚመጡት በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ በዓመፃ የተቀመጡትንና የሚቀመጡትን «ከወንበር ዉረዱ፣ እኛ እንቀመጥበት» ብለዉ ሳይሆን፤ የእግዚአብሔር ቁጣ በእያንዳንዱ ዓመፀኛ የዓለም መንግሥታት፣ ባለሥልጣናት፣ ድርጅት፣ ቡድንና ግለሰብ ላይ ስትነድ፤ ያኔ

«አባኪቸሁ እናንተ የእግዚአብሔር ባለሟሎችና እንደራሴዎች ኑና ወንበሩን ተረከቡ፣ የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ጠብቁ፣ አገልግሉ፣ በአራቱም ማእዘን እግዚአብሔር ያዘዛችሁን ፈቃዱን ፈጽሙ» ተብለዉ በመለመን ነዉ። እነሱም እግዚአብሔር «ዉጡ፣ ወንበሩንም ተረከቡ» ብሎ ሲያዛቸዉ ብቻ ነዉ ወደ እዉነተኛዉ ወንበር መተዉ ራሳቸዉን የሚገልጹት እንጂ፤ አንዳች የሥልጣን ሆነ የጥቅም ፍላጎት የሌላቸዉ፣ ነገረ መስቀሉ በሕሊናቸዉ የሚደማ፣ የአደራ እናታቸዉ የእመ አምላክ ድንግል ማርያም መሪር ኀዘን በሕሊናቸዉ የሚያነባ፣ አንዳች የተለየ ክብር፣ ዝና፣ ግነት የማይፈልጉ፤ ያ ፍቅሩን ራቁቱን በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ለሰዉ ዘሮች የገለጸዉን፣ ሕይወት እንዲሆናቸዉ ቅዱስ ሥጋዉን በመቁረስ ክቡር ደሙን በማፍሰስ ለሰዉ ዘሮች በሙሉ የሰጠዉን፣ አልፋና ዖሜጋ የሁሉ ጌታና ፈጣሪ የሆነዉን ልዑል እግዚአብሔር በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ እንዲመለክ፣ እንዲመሰገን፣ እንዲገን ነዉ ጸሎታቸዉና ፍላጎታቸዉ። እንዲሁም ሌላዉ ተግባራቸዉ የአዳምና ሔዋን ዘሮች ሁሉ የሕይወታቸዉ ምስጢር ቁልፍ የሆነችዉ የአደራ እናቸዉንና እመቤታቸዉን ድንግል ማርያም እንደ ልጇ መድኃኔዓለም በአራቱም ማእዘን እንድትመሰገንና እንድትገን ማድረግ ነዉ። ከዚህ ጋርም የእግዚአብሔር ትእዛዝ እንዲጠበቅ፣ ፈቃዱ በአራቱም ማእዘን እንዲፈጸመ ማድረግና ማስደረግ ነዉ ዋና ዓላማቸዉ እንጂ፤ ፍጡሩ ሰዉ የሆነዉ እንዲመለክና እንዲገን ማድረግ አይደለም።

የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖትና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን፤ ቅዱሳን መልእክትን፣ ቅዱሳን ነቢያትን፣ ቅዱሳን ሐዋርያትን፣ ቅዱሳን ሰማዕታትን፣ ቅዱሳን ጻድቃንን በሚገባ የምታከብራቸዉና በወር ዉስጥ ያሉትን ቀናተ በስማቸዉ ሰይማ የምታስባቸዉ፤ አገልጋዮች ሆኑ ምእመናን በረከትና ጸጋ እንዲያገኙ ነዉ። ከዚያ ዉጭ ግን ከቅዱሳን መላእክት ሆነ ከነቢያት፣ ከሐዋርያት፣ ከሰማዕታት፣ ከጻድቃን ለይተዉ በተለየ ሁኔታ እንዲገን የሚያደርጉት ቅዱስ የለም። እያንዳንዱ ግለሰብ እንደተደረገለት ዉለታ በግሉ የሚያገነዉና በተለየ ሁኔታ የሚያስበዉ ቅዱስ ወይንም ቅድስት ሊኖረዉ ይችላል። እንደ አጠቃላይ ግን ከእግዚአብሔር እንደተሰጣቸዉ ክብርና ማእረግ እያንዳንዱ ሊያከብራቸዉና ሊያስባቸዉ ይገባል። በመሆኑም ቅዱስ ነቢዩ ኤልያስ እንደሌሎቹ ቅዱሳን በምልጃዉ ይራዳናል፤ ጥብቅና ይቆምልናል እንጂ በተለየ ሁኔታ ከሰማይ መቶ የሰዉ አኗኗር እየኖረ በዚህች ምድር ዉስጥ አይመላለስም። እኔም ስለ እግዚአብሔር ሙሉ እዉነት እግዚአብሔር እንድመሰክር ያስደረገዉ፤ በአገልጋዮች ሆነ በአማኞች ዘንድ አታላዩ(ሸዋጁ) የዲያብሎስ መንፈስ ክፍፍል እንዳያመጣና ሰዎች እንደ ሥጋና ደሜታቸዉ ተነሥተዉና በአታላዩ(ሸዋጁ) መንፈስ ተታለዉ «እኔ ነኝ የተቀባሁት ሣልሳዊ ቴዎድሮስ (ርእሰ ነገሥት)፣ እኔ ነኝ ካህኑ እጨጌ (ፓትርያርክ)»

እያሉ ሕዝቡንና ምእመኑን እንዳያሳስቱና እንዳያሰናክሉ ነዉ:: እንዲሁም ከጥንት እስከ ሕይዉነት ዘመን አንድ ቀን ድረስ ስለነበረዉና እየሆነ ስላለዉ እንዲሁም ወደፊትም ስለሚሆነዉ የእግዚአብሔርን ሙሉ እዉነት ለዓለም እንድገልጽ ነዉ:: እግዚአብሔርም ለዚህ ነዉ ያስነሳኝና በተለያየ ጊዜ መልእክታቱን እንዳደርስ ያስደረገዉ::

ሌላዉ መታወቅ ያለበት «ሰንበት ሻረ፣ ከእግዚአብሔር አይደለም፣ የሙሴን ሕግ የሻረ ነዉ... ወዘተ» በማለት የሰንበትን ጌታና የሙሴን አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስን የወነጀሉትና ያሰቀሉት አስመሳይ አገልጋዮች ጸሐፍት፣ ፈሪሳዉያን፣ የአይሁድ ካህናት አለቆችና ካህናት፤ «እኛ እዉተነኛ የእግዚአብሔር አገልጋዮችና እንደራሴዎች ነን» ቢሉም፤ የእያንዳንዱን የዉስጥም የዉጭም ሕይወት የሚያዉቀዉ አምላክ አጠገባቸዉ ነበርና ለሕዝቡ «ጽድቃችሁ ከእነዚህ ከአስመሳይ አገልጋዮች ጸሐፍት ፈሪሳዉያን ካልበለጠ በስተቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አትገቡም» በማለት ነዉ የአስመሳዮቹ አገልግሎት ሆነ ሕይወት እዉነተኛ አገልግሎትና ሕይወት አንዳልሆነ የመሰከረበቸዉ:: አሁንም የእነሱን አገልግሎትና ሕይወት ትዉልዱ እንዲይዝ ለማድረግ የሚጣረዉ ጥረት ሆነ ምስክርነት ለእዉነትኛ አገልግሎትና ሕይወት እንደማያበቃን በሚገባ አስተዉለን፤ አገልግሎታችን ሁሉ በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ የሆነ፤ ሕይወታችንም ቅንነት፣ እዉነተኛነት፣ ታማኝነት፣ የዋህነት፣ ልባምነት፣ ትህትና፣ ፍቅር የተላበሰ መሆን ይኖርበታል::

ሌላዉ መታወቅ ያለበት ደግሞ ከክርስቶስ መወለድና መሰቀል በፊት መስቀል የመርገም ምልክት ነበር:: ኮከብ የሚመስለዉ ደግሞ በአንድ አምላክ የሚያምኑ ምልክት ነበር:: በአዲስ ዘመን ግን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ቅዱስ ሥጋዉን ከቆረሰበትና ክቡር ደሙን ካፈሰሰበት በኋላ ግን መስቀል፤ የመልከ ጼዴቅ፣ የአብርሃም፣ የይስሐቅ፣ የያዕቆብ፣ የሙሴ አምላክን የሚያምኑ አማኞች ዋና መለያቸዉና ምልክታቸዉ ሆኗል:: በተቃራኒዉ ደግሞ ኮከቡ በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወትና አገልግሎት ዉስጥ ዲያብሎስ እንደ ዓርማነት የሚጠቀመዉ ሆኗል:: በመሆኑም በዘመነ ሐዲስ መስቀልና ኮከብ አንዳች አንድነትና ኅብረት የሌላቸዉ ናቸዉ:: እንዲሁም የአዲስ ዘመን መለኮታዊ ዓርማችንም የኢየሱስ ክርስቶስ መለያ የሆነዉ «አሸናፊ አንበሳ» ብቻ ነዉ::

«ሣልሳዊ ቴዎድሮስ» በመባል የሚጠበቁትን እግዚአብሔር ለእዉነተኛ አገልጋዮቹና መልእክተኞቹ የገለጸዉ፤ ካህንና ርእሰ ነገሥት መሆናቸዉን ነዉ:: እንዲሁም ከ**1998** ዓ.ም ጀምሮ አሁን እያለ ስላለሁና ወደፊትም ስለሚሆነ በግልጽ እግዚአብሔር ገልጾላቸዉ «ኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን» በሚል ርእስ እስከ መስከረም **21/2004** ዓ.ም ድረስ አምስት

መልእክት ለኢትዮጵያዉያንና ለዓለም ያስተላለፉት ናቸዉ ካህን ወ ርእሰ ነገሥት እንጂ፤ «ጳጉሜ 1/2003 ዓ.ም ከሰማያት ወረደ» የተባለዉ ርእሰ ነቢያትና ርእሰ ነገሥት ኤልያስ አይደለም። እኝህ ኢትዮጵያዊ ለቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያና ለዓለም ለእንደራሴነት የተመረጡትና የተቀቡት ካህኑ ርእሰ ነገሥት፤ እንደ ነቢዩ ኤልያስ ከዛም በላይ በዓለም ላይ ሆነ በዓመፀኞች ላይ መቅሰፍትንና መዓትን ማምጣት የሚችሉ፣ ምሕረትም ከለመኑ ከእግዚአብሐር ዘንድ የሚደረግላቸዉ፣ በአሁን ዘመን እግዚአብሔር ያስነሣቸዉ የኢትዮጵያዊ ሰዉነት የተላበሱ የቅዱስ ኪዳኗ የኢትዮጵያ ዜጋ የሆኑ አባት ናቸዉ እንጂ ከሰማይ የወረዱ አይደለም።

እንግዲህ ባለማወቅና ባለማስተዋል ለጨለማዉ ገዥ መከፋፈያና ማደናገሪያ ተግባር ላይ የተሰማራን ሰዎች፤ ወደ እግዚአብሔር ሙሉ እዉነት በመምጣት ለእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ እንመላለስ። በዓለማ የእግዚአብሔርን መንግሥት ማለትም ቤተሕዝቡ፣ ቤተክህነቱ፣ ቤተምልክናዉ ተዋሕደዉ በአንድ መንፈስ ቅዱስ የሚመራበትን የቅዱሱ ኪዳን ሥርዓት ለማስቀረትና የራስን የሥጋና የደም ስሜትና ዓላማ ለማሳካት የምንመላለስ ከሆነ ደግሞ፤ የዓመፃ ልጆች በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ እጅግ እጅግ በቅርብ ጊዜ ዉስጥ ከምድር ሲጠረጉና ሲጸዱ፤ እኛም አብረን እንደምንጠረግና እንደምንጸዳ በሚገባ ልናዉቅና ልናስተዉል ይገባል። በቅርቡ እግዚአብሔር በኢትዮጵያ ሆነ በዓለም የሚዘረጋዉን ሰማያዊ ሥርዓት ማንም ሆነ ማን ሊያስቀረዉ አይደለም አንድ ቀን ማዘግየት አይችልም። ይላል ታናሹ ልጃችሁና ወንድማችሁ። <teklekidan979@yahoo.com>

ወስብሓት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ማርያም

እግዚአብሔር ቅዱስ ኪዳኗን ኢትዮጵያን ይባርክ፤ የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖታችንን ይጠብቅ።

<u>ግልባጭ</u>

† ለእዉነተኛዉ ለእግዚአብሔርና ለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ባለሚልና እንደራሴ

<u>ኢትዮጵያዊዉ ካህኑ እጨጌ(ፓትርያርክ)።</u>

† ለእዉነተኛዉ ለእግዚአብሔርና ለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ባለሚልና እንደራሴ

<u>ኢትዮጵያዊዉ ካህኑ ርእሰ ነገሥት(ንጉሠ ነገሥት)</u>

ኅዳር ፲፪÷፳፻፫